Profile

*የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር የክቡር አቶ እንዳሻው ጣሰው መልዕክት፡-*

*ብልጽግና ፓርቲ እና በፓርቲው የሚመራው መንግስት ተግባራዊ ካደረጋቸው የሪፎርም እርምጃዎች መካከል አንዱ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አውን መሆን ተጠቃሽ ነው፡፡ በህብረ ብሄራዊ የፌዴራሊዝም ስርዓቱ ማዕቀፍ የተፈቀደውን ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ለመመለስ ብልጽግና ፓርቲ እና በፓርቲው የሚመራው መንግስት ያሳዩት ቁርጠኝነት ውጤት ነው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል እና ሌሎችም በቀድሞው የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሲተዳደሩ ለበሩት መዋቅሮች የተሰጠው ክልል የመሆን ጥያቄ ምላሽ፡፡*

*ነሀሴ 13 ቀን 2015 ዓመተ ምህረት ላይ የተመሰረተው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የህብረ ብሄራዊ ፌዴራሊዝም ስርዓቱን ከመሰረቱት የክልል መንግስታት አንዱ በመሆን ጠንካራ ሀገር እና ሀገረ መንግስት በመመስረቱ ሂደት የበኩሉን ሚና በታላቅ የሃላፊነት መንፈስ እየተወጣ ይገኛል፡፡*

*የጉራጌ፣ የሀዲያ፣ የስልጤ ፣ የካምባታ፣ የሀላባ ፣ የጠምባሮ፣ የየም፣ የማረቆ፣ የቀቤና እና የዶንጋ ብሄረሰቦችን እና ሌሎችንም ህዝቦች በማቀፍ የተደራጀው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በጋራ እሴቶች የተሳሰረች፣ በጋራ ትርክት የጸናች፣ በጋራ ህልም ተስፋዋን ከፍ ለማድረግ የምትተጋ ህብረ ብሄራዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ከወትሮው በላቀ የታታሪነት ፣ የስራ ፈጣሪነት መንፈስ ለመንቀሳቀስ ቃላቸውን አድሰው ተነስተዋል፡፡*

*በህብረ ብሄራዊ ፌዴራሊዝም ስርዓቱ የተደነገጉ የራስ አስተዳደር እና የጋራ አስተደዳደር ማዕቀፎችን መሰረት አድርጎ በመንቀሳቀስ ፣ ማንነት እና ኢትዮጵያዊ አንድነት ሚዛናቸውን ጠብቀው የሚራመዱባት ኢትዮጵያን እውን በማድረጉ ሂደት የእያንዳንዳችን ድርሻ ወሳኝ በመሆኑ መላው ዜጎች የየበኩላቸውን እንዲያበረክቱ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ አቀርባለሁ፡፡*

*ዘላቂ ሰላም ፣ ለዘላቂ ልማት እና ለዘላቂ ሀገር ግንባታ መሰረት በመሆኑ መላው ህዝባችን ሰላሙን ለማጽናት፣ ልማቱን ለማፋጠን በቁርጠኝነት እና  በጋራ መረባረብ በሚጠበቅበት ወቅት ላይ መሆኑንም ለማስታወስ እወዳለሁ፡፡*

*ሀገራችን ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ የመልሚያ አቅሞችና ጸጋዎች ባለቤት የሆነች ብሩህ ተስፋ ያላት ሀገር ናትና የምግብ  ዋስትና ሉዓላዊነትን በጋራ ትጋት እውን በማድረግ ሉዓላዊነቷ እና ብሄራዊ ክብሯ የተሟላ እንዲሆን የጀመርነውን ጥረት እናጠናክር! ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ የምትከበር እና የምትፈራ ሀገር እንድትሆን በሁሉም መስኮች ርብርብ እናድርግ!*

*አመሰግናለሁ!*

2./ **የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምስረታ እና  አጠቃላይ ገፅታ**

**2.1/ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምስረታ**

በ2015 ዓመተ ምህረት በተካሄደው ህዝብ ውሳኔ ውጤት መሰረት የቀድሞው የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል አካል የነበረው የደቡብ  ኢትዮጵያ ክልል 12ኛው የፌዴሬሽኑ አባል  ክልል ሆኖ እንዲደራጅ በኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት  መወሰኑን ተከትሎ ፤ በቀድሞው የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሲተደደሩ የነበሩት ቀሪዎቹ  የጉራጌ፣ የሀዲያ፣ የስልጤ፣ የካምባታና ጠምባሮ፣ የሀላባ ዞኖች እና የየም ልዩ ወረዳ  ሪፎርም በማድረግ በጋራ በአንድ ክልል እንዲደራጁ በተወሰነው መሰረት **የማዕከላዊ** ኢትዮጵያ ክልል መንግስት  ነሀሴ 13 ቀን  2015 ዓመተ ምህረት ተመሰረተ፡፡

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአዋጅ ቁጥር 1/1987 ዓ.ም. አንቀጽ 47 መሠረት ከተመሰረቱት ክልሎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ክልሉ የሚገኘዉ በኢትዮጵያ ማዕከላዊ አቅጣጫ ሲሆን ብዝሃ ማዕከላት እንዲኖሩት ተደርጎ  የተዋቀረ ሲሆን የመስተዳድር ምክር ቤት መቀመጫው ሆሳዕና ከተማ ነው፡፡

## 2.2/ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምስረታ አጠቃላይ ገፅታ

የክልሉ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ከ7⁰04’ እስከ 8⁰03’ ሰሜናዊ ኬክሮስ እና ከ37⁰20’ እስከ 38⁰60’ ምሥራቃዊ ኬንትሮሰ ላይ ነው፡፡ አዋሳኞቹም በሰሜን፣ በምእራብና በምስራቅ አቅጣጫ ከኦሮሚያ ክልል፤ በደቡብ በኩል ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በደቡብ ምዕራብ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ይዋሰናል፡፡ አስተዳደራዊ መዋቅሩም በዞኖች፣" በልዩ ወረዳዎች፣" በወረዳዎች፣" በከተማ አስተዳደሮችና በቀበሌዎች የተደራጀ ነው:: ክልሉ **1,515,.600** ሄ/ር ስፋት ያለው ሲሆን ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት **1.38** በመቶውን የሚይዝ ነው፡፡

የሕዝብ ብዛት በተመለከተ በ1999 ዓ.ም. የብሔራዊ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መረጃ ፕሮጀክሽን መሠረት የክልሉ የሕዝብ አማካይ አመታዊ ዕድገት ምጣኔ 2.9 በመቶ ነው።

የሕዝብ ዕድገት ምጣኔዉ በመኖሪያ አካባቢ በተመለከተ የገጠር ሕዝብ አመታዊ ዕድገት በ2.8 በመቶ ሲሆን በከተማ የሕዝብ የዕድገት ምጣኔ 4.8 በመቶ ነዉ ። በዚህ መሰረት በ2015 ዓ.ም. የክልሉ ሕዝብ 7,039,772 ይገመታል፡፡ ከዚህ ውስጥ 80.7% በገጠር እና ቀሪዉ 19.3 % በከተሞች የሚኖር ነው፡፡ ይህም ከአገሪቱ አጠቃላይ ህዝብ 6.47 በመቶውን የሚሸፍን ሲሆን የክልሉ አማካይ የህዝብ ጥግግት ደግሞ 464 ሰዎች በካሬ ኪ.ሜ ነው።

ክልሉ በአሁኑ ወቅት በ7 ዞኖች/ ሀዲያ፣ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ካምባታ፣ ሀላባ፣ የም ዞኖች/፣ በ3 ልዩ ወረዳዎች/ ጠምባሮ፣ ማረቆ ቀቤና ልዩ ወረዳዎች/ ፣ በ50 ወረዳዎች እና በ29 የከተማ አስተዳደሮች የተከፈለ ነው። ክልሉ 1294 ቀበሌዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህም 185 የከተማ 1109 የገጠር ቀበሌያት ናቸው፡፡

### 2.3 / የክልሉን ስነምህዳር በተመለከተ

የማዕከላዊ የኢትዮጵያ ክልል በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የአየር ንብረቶች ይዟል በሚባል ደረጃ ለኑሮ ምቹ የሆኑ የደጋ፣ የወይና ደጋ እና የቆላ አከባቢዎች ያሉት ሲሆን በሁለት የተራራቁ

ጫፎች ያለው የአየር ንብረትም በክልሉ የተለያዩ ስነምህዳር (ecology) የተፈጥሮ ሀብቶች፣ የተለያዩ የግብርና ሥርዓቶች፣ የአኗኗርና የባህል ብዝሀነት እንዲኖር አድርጓል፡፡

የክልሉ ከፍተኛ ሥፍዎች እንደ ዘቢዳር፣ሙጎና አምባሪቾ ተራራዎች ሲሆኑ ዝቅተኛው ሥፍራ ደግሞ በጠምባሮ ልዩ ወረዳ በኦሞ ወንዝ አቅራቢያ ባለው የኦሞ ሸለቆ ጫፍ ከባህር ጠለል በላይ 447 ሜትር ከፍታ ያለው ሥፍራ ነው፡፡

## 2.4/ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መሰረቶች

**የግብርና ውጤቶች፡-**

የክልሉ ብሔረሰቦች ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረት ብዝሀነት ያለው የግብርና ሥርዓት (diversified agricultural systems) ነው፡፡ በክልሉ የግብርና ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው የእርሻ ሥራ ሲሆን የእንስሳት እርባታም ጎን ለጎን ይካሄዳል፡፡ በክልሉ በዋነኛነት የሚመረቱ የብርዕና አገደ ሰብሎች (በቆሎ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ) ጥራጥሬዎች (አተር፣ ባቄላ፣ ሽምብራ)፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎች (ሙዝ፣ አቮካዶ፣ ማንጎ፣ አፕል፣ አናናስ)፣ የስራ ስር ሰብሎች (እንሰት፣ድንች፣ ጎደሬ)፣ እንዲሁም ቡና፤ ዝንጅብል እና የተለያዩ ቅመማ-ቅመሞች ወዘተ ናቸው፡፡

## 2.6/ የጤና ተቋማትና አገልግሎቶች

በ2014 ዓ.ም የክልሉ ጤና ሽፋን 79 % ሲሆን ግንባታቸዉ ተጠናቅቆ አገልግሎት መስጠት የጀመሩ አዳዲስ ተቋማትን ጨምሮ በክልሉ በአጠቃላይ 24 ሆስፒታሎች፣ 216 ጤና ጣቢያዎች፣ 1178 ጤና ኬላዎችና **272 ክሊኒኮች (ሁሉም ዓይነት)** ይገኛሉ፡፡

## የትምህርት ተደራሽነት

በ2014 ዓ.ም በክልሉ መንግስት የሚተዳደሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች(ከ1-8) በጥቅሉ 1750፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች(9-12) 260፣ እና ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች 6፣ የቴክኒክና ሙያ ትም/ናሥልጠና ኮሌጆች 27 የደረሰ ሲሆን፤ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚተዳደሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች(ከ1-8) 213 እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ(9-12) 22፤ የግል ትም/ና ሥልጠና ኮሌጆች 30፣ የመምህራን ትም/ኮሌጅ አንድ 1፣ ጤና ኮሌጅ አንድ ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ በመንግስት የሚተዳደሩ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አንጻር ሦስት ዩኒቨርሲቲዎችና ካምፓሶች ይገኛሉ፡፡

## የመንገድ መሰረተ ልማት ሽፋን፡-

በክልሉ እስከ 2014 ዓ.ም ግንባታዉ ተጠናቅቆ ርክክብ የተደረገ ክልላዊ ጥቅል የመንገድ መሰረተ ልማት ሽፋን 4983.25 ኪ.ሜ ሲሆን ይህም 2028 ኪ.ሜ በደቡብ መንገዶች ባለስልጣን፣ 1791.9 ኪ.ሜ በትራንስፖርትና መንገድ ልማት ቢሮ የሁ/አቀ/ገ/ተ/መ/ፕ፣ 699.4 ኪ.ሜ የአስፓልት መንገድ እና ቀሪዉ 464 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ በፌደራል መንገዶች ባለስልጣን የተገነባ ነው። በዚህ ስሌት መሰረት ክልላዊ ከሁሉ አቀፍ የገጠር ተድራሽ መንገድ ውጭ ክልላዊ የመንገድ ጥግግት 210.06 ኪ.ሜ/1000] ካሬ .ኪ.ሜ መሆኑን ማየት ይቻላል።

## የከረሰ ምድር ማእድን እና የኮንስትራክሽን ግብአት እምቅ ሀብት

የከርሰ ምድር የማዕድን ሃብትን በተመለከተ ሀገር አቀፍ የጂኦሎጂካል ሰርቬይ መረጃ እና የተፋሰስ የማስተር ፕላን ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የከርሰ እና የገጸ ምድር ማዕድን ክምችት መኖሩ ተለይቷል። ለኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ሊውሉ የሚችሉ እንደ ክሌይ፣ የድንጋይ ከሰል፣ የብረት ማዕድን ፣ የጌጣ ጌጥና የግንባታ ማዕድናት ይገኛሉ። ጉራጌ፣ ሃዲያ እና የም ዞን ካኦላይን፣ ላይም ስቶን ደግሞ በጉራጌ ዞን የሚገኝ ሲሆን መጠናቸውም ወደ ኢንዱስትሪ ሰኬል መግባት የሚያስችል እንደሆነ መረጃው ያመለክታል። አሸዋ፣ ጥርብ ድንጋይ፤ የኖራ ድንጋይ እና የመሳሰሉት የኮንስትራክሽን ግብአቶች በክልሉ በተለያዩ አከባቢዎች በስፋት ይገኛሉ። ከዚህም ባሻገር በኮንስትራክሽን ሙያ ዘርፍ የረጅም ጊዜ ልምድና እውቀት ያላቸው፤ በቁጥራቸውም እጅግ ብዛት ያላቸው ሙያተኞች የሚገኙበት ክልል በመሆኑ የኮንስትራክሽን ሥራ ለማከናወን በእጅጉ አመቺ ነው።

የድንጋይ ከሰል ከፍተኛ የሀይል ፍጆታ ለሚፈልጉ ለብረታ ብረት፣ ለስሚንቶና ለሴራሚክስ ኢንዱስትሪ ዋና የሀይል ምንጭ ሆኖ ስለሚያገለግል ለኢንዱስትሪ ልማቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

## የመስኖና እና ንጹህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት

ከመስኖ አቅም አኳያ በአነስተኛ ግድብ /Micro and Min Dams/ ሊለሙ የሚችሉ ወንዞች፤ በሃዲያ ዞን አመካ፣ ገሙና፤ እና ጎምቦራ ወንዞች፣ በጉራጌ ዞን ዊንቁ፣ ዋቤ፤ አንዘቻ፤ ደጎስ ወራቤሳ፣ ዳጌ፤ ጎግዋሬ እና ዋልጋ ወንዞች፤ በሀላባ ዞን የሚገኘው የብላቴ ወንዝ በሰልጤ ዞን የሚገኘው የዲጆ ወንዝ እንዲሁም የጊቤ ወንዝ አቅም ያላቸው ተጠቃሽ የክልሉ ሀብቶችት ናቸው። ከመጠጥ ውሀ አቅርቦት አንጻር በ2014 ዓ.ም በተካሄደዉ የንጹህ የመጠጥ ውሃ ተቋማት ቆጠራ እና የአቅርቦት ሽፋን ጥናት መሰረት ክልላዊ አማካይ የንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን 49%. ደርሷል።

## የኃይል አቅርቦትን በተመለከተ

የማእከላዊ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም የተገነቡና በመገንባት ላይ ያለን ጨምሮ አምስት የኃይል ማስተላለፊያ ሳብስቴሽን ያሉት ሲሆን በአገልግሎት በግብርና በተለይም በኢንዳስትሪ ዘርፍ ለሚሰማሩ የግል ባለሁብቶች የማያቋርጥ የኃይል አቅርቦት የሚቀርብበት በመሆኑ የክልል የኢንቨስትመንት ተወዳዳሪነት ከሌሎች አከባቢ በተለየ ሁኔታ ከፍ ያደርገዋል፡፡

ክልሉ ለኢንዱስትሪዎች የሃይል ምንጭ ከሚሆኑት ዘመናዊ የሃይል ምንጮች ኤሌክትሪክ አንዱ ሲሆን የኤሌትሪክ አገልግሎት ክልላዊ ስርጭቶች /ICS/ እርስ በርስ በተያያዙ ሲስተም ተዘርግተዋል፡፡ ክልሉ በ2014 ዓ.ም. ከተሞችና መንደር ማዕከላት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያገኙ ናቸው፡፡ *(የመረጃው ምንጭ ፓሳን ቢሮ)*

## 2.6/ የክልሉ ሰው ኃይል ለኢንቨስትመንት ያለው ምቹ ሁኔታ

በየትኛውም የኢንቨስትመንት ዘርፍ ተቀጥረው መስራት የሚችሉ ከፍተኛና መካከለኛ ሙያ ያላቸው ዜጎች በማያቋርጥ ሁኔታ እያፈራ ያለ ክልል በመሆኑ ለየትኛውም የኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚሆን የሰው ኃይል ፍላጎት በቀላሉ ማግኘት የሚቻልበት ክልል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክልሉ ተወላጅ ዜጎች ልዩ መለያ የሆነው ሥራ ወዳድነት እና ታታሪነት እንዲሁም የሀገር ውስጥ የሰው ኃይል ፍላጎትን ማሟላት እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ የአለም ሀገራትና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ከየትኛውም አከባቢ በተለየ ሁኔታ ተንቀሳቅሰው የሚሰሩ በመሆናቸው በክልሉ ውስጥ በየትኛውም የኢንቨስትመንት ዘርፍ በግብርናም ይሁን በተለይም በኢንዳስትሪ ዘርፍ ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች ምርቶቻቸውን በቀላሉ በውጭና በሀገር ውስጥ ገበያዎች ለመሸጥ የሚያስችላቸው ልዩ እድል ያለበት ክልል ነው፡

## ዲያስፖራው ለክልሉ ኢንቨስትመንት ያለው ሚና

*ዲያስፖራ ሁሌም እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ልምዶችና እውቀቶችን የማግኘት ዕድሉ ሰፊ በመሆኑ ዕውቀቱን፣ ልምዱን እና የቢዝነስና ኢንተርፕሪኒርሽፕ ዕውቀቱን ወደ ሀገሩ በማምጣት ከፍተኛ ለውጥ መፍጠር የሚችል ሀይል ነው፡፡ በተለይም በኢንዱስትሪ ካልበለጸጉ ሀገሮች ወደ ኢንዱስትሪ የበለጸጉ ሀገሮች የሚሄዱ ዲያስፖራዎች በታዳጊ ሀገራቸው የኢንዱስትሪ ልማት ሽግግር እንዲፋጠን ሊያደርጉ የሚችሉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሚሆን ይታመናል፡፡*

*ዲያስፖራዎች ንግድና ኢንቨስትመንትን እንዲሁም ቱሪዝምን በማስተወቅና በማነቃቃት በኩል ያላቸው ድርሻ እጅግ ጉልህ ነው፡፡ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በተመለከተ ዲያስፖራው ሁልጊዜም ጠቃሚ እውቀትና ልምድ ያለው በመሆኑ ይህንን ጠቃሚ ልምዱንና እውቀቱን ወደ ሀገሩ የማምጣት ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡ ዳያስፖራ የውጭ ቴክኖሎጂን በመኮረጅ ለሀገሩ ለአሁኑና ለቀጣይ ትውልድ በማሸጋገር እንዲሁም በሰብዓዊ ልማት ላይ ትልቅ ስራ ይሰራል፡፡*

ዳያስፖራው የገንዘብ አቅም ያለው፣በውጭ ቆይታው የሥራና የዕውቀት ልምድ የወሰደና ምርቱን የት አምርቶ የት እና እንዴት ቢሸጥ ውጤት እንዲያመጣ በቂ ልምድና እውቀት ያለው ኃይል በመሆኑ መዋለ ንዋዩን በድፍረት የማፍሰስ አቅሙ ከፍ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶችና ለውጭ ዜጎች አርዓያ በመሆኑ በትውልድ አከባቢው መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ያደርጋል፡፡ የማእከላዊ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የዳያስፖራ አባላት በአውሮፓ ኤዢያ፣ አፍሪካ፣ አውስትራሊያ፣ ካናዳ፣ አሜሪካ በጥቅሉ በመላው አለም ውስጥ በሰፊው ተሰራጭተው የሚኖሩ በመሆኑ የውጭ ኢንቨስትመንትን በመሳብ፤ መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ እና ቴክኖሎጂን ወደ አዲሱ ማእከላዊ ክልላችን በመሳብ በኩል ከፍተኛ የክልሉ ኢንቨስትመንት አቅም እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.7/ የኢንዳስትሪ ጥሬ እቃ አቅርቦትን በተመለከተ

ክልሉ ለተለያዩ የአግሮ ፕሮሰሲንግ አገልግሎት የሚውሉ የግብርና ውጤቶች የማምረት ከፍተኛ አቅም አለው ለአብነትም በክልሉ በዋነኛነት ከሚመረቱ የብርዕና አገደ ሰብሎች በቆሎ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ ከጥራጥሬዎች አተር፣ ባቄላ፣ ሽምብራ፣ ከተለያዩ ፍራፍሬዎች ሙዝ፣ አቮካዶ፣ ማንጎ፣ አፕል፣ አናናስ፣ ከስራ ስር ሰብሎች እንሰት፣ድንች፣ ጎደሬን ከቅባት እህሎች ደግሞ ኑግ፣ሱፍ፣ሰሊጥና ቦሎቄ ከአትክልት ቲማቲምና ሽንኩርትን መጥቀስ ሲቻል ለቡና፤ ለዝንጅብል፣ ለሮዝሜሪ እና ለተለያዩ ቅመማ-ቅመሞች ወዘተ ተስማሚ የአፈርና አየር ንብረት የሚገኝበት ክልል ነው፡፡ ለኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ሊውሉ የሚችሉ እንደ ክሌይ፣ የድንጋይ ከሰል፣ የብረት ማዕድን፣ካኦላይን፣ ላይም ፣ የጌጣ ጌጥና የግንባታ ማዕድናት በክልሉ ይገኛሉ፡፡ አሸዋ፣ ጥርብ ድንጋይ፤ የኖራ ድንጋይ እና የመሳሰሉት የኮንስትራክሽን ግብአቶች በክልሉ በተለያዩ አከባቢዎች በስፋት ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክልሉ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ የኢንዳስትሪ ጥሬ እቃ የሚሆኑ ልዩ ልዩ የግብርና ውጤቶች እና የተፈጥሮ ማእድኖች በከፍተኛ ደረጃ ከሚገኝባቸው ክልሎች ከኦሮሚያ፣ደቡብ ኢትዮጵያና ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ጋር የሚዋሰን በመሆኑና ለአዲስ አበባባና ለሞጆ ደረቅ ወደብ ካለው ቅርበት አንጻር ከሌሎች አከባቢዎች በተሻለ ሁኔታ የኢንዳስትሪ ጥሬ እቃዎች ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ገበያ ለማስገባት ልዩ እምቅ አቅም ያለው መሆኑ ክልሉን ፍጹም ተወዳዳሪ ያደርገዋል፡፡

## 2.9 የክልሉ ቱሪዝም ኢንቨስትመንት እምቅ አቅም

ክልላችን ታይተው የማይጠገቡ በርካታ የቱሪስት መስህቦች ያሉበት ክልል ነው፡፡ ለአብነትም በዩኒስኮ የተመዘገበ እና ለመመዝገብ በሂደት ላይ ያሉ የማይዳሰሱና የሚዳሰሱ ቅርሶች፤ ሀይማኖታዊና ታሪካዊ መስህቦች እና ብሔራዊ ፓርክ የሚገኙበት ክልል ነው፡፡

### ጥንታዊ፣ ታሪካዊና ሀይማኖታዊ ቅርሶች

በክልሉ ታሪካዊ ቅርሶች ውስጥ ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኘው ጢያ ትክል ድንጋይ መካነ ቅርስ ሲሆን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት ሳይንስና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በቅርስነት የተመዘገበ ነው፡፡ የጢያ መካነ ቅርስ የሚገኘው በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ በጢያ ልዩ ቀበሌ ሲሆን ከአዲስ አበባ ከተማ ደቡብ ምዕራብ 88 ኪ/ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ መካነ ቅርሱ ከመልካ ቁንጡሬ የአርኪዎሎጂ መካነ ቅርስ የሚርቀው 50 ኪሎ ሜትሮች ብቻ ነው፡፡ የጢያ መካነ ቅርስ ትክል ድንጋዮች በቁጥር ወደ 44 የሚደርሱ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 32 ያህሉ ልዩ ልዩ ቅርጾችና ምስሎች ያሉባቸው ናቸው፡፡ በድንጋዮቹ ላይ የተቀረጹ ምስሎችም የጉራዴ ወይም የሰይፍ ወይም የጩቤ፣ የጦር፣ የትራስ እንጨት፣ ክብ ወይም ጸሐይ መሰል ቅርጾች፣ የግማሽ ጨረቃ ምስሎች፣ እጆቹን ወደ ላይ የዘረጋ የሰው ክንዶች የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የአርኬኦሎጂ አጥኚዎች እንደሚሉት የጥያ ትክል ድንጋዮች ከሰሃራ በታች ካሉት ትክል ድንጋዮች ከአክሱም በስተቀር በዕድሜ የሚበልጣቸው እንደሌለ በመጥቀስ ቦታው እ.ኤ.አ. ከ1980 ጀምሮ በዓለም የቅርስ መዝገብ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

በክልሉ ውሰጥ ከሚገኙ የተለያዩ ጥንታዊና ሀይማኖታዊ ቅርሶች ውስጥ ምሁር ኢየሱስና፣ ምድረከብድ አቦ ገዳማት (በጉራጌ)፣ ስልጢ ዞን ያለውን ጥንታዊ የአልከሶ (ሀጅ አልዬ) መስጊድ እና በጉራጌ ዞን የሚገኘውን የአብሬት ታሪካዊ መስጊድ በየም ዞን የሚገኘው የአንጋሪ ቤተ መንግስት እና ባህላው መድሃኒት አሰባሰብ መጥቀስ ይቻላል፡፡

## የተፈጥሮ መስህቦች

በክልሉ ለቱሪስት መስህብነት የሚያገለግሉ በርካታ ፏፏቴዎች የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ በከምባታ ዞን የአጀራ መንታያ ፏፏቴ፣ በስልጢ ዞን የሚገኙት ወይራ፣ ውሊጮ፣ ላምሬ እና ጨፋሬ ፏፏቴዎች፤ በሐድያ ዞን የሚገኙት ሃቢቾ፣ ፊንጪዋ፣ አጋሜ እና አሊዳ ፏፏቴዎች፤ በየም ዞን የሚገኙት፤ የወማ ፍል ውሃ፤ የብርበርሳ ፏፏቴ፤ የዞፍካር ትክል ድንጋዮች የቦር ተራራ በምስራቅ ጉራጌ ዞን የሚገኘው የአለልቱ ፏፏቴ እና ሀያ ስድስት ኪሎሜትር በምድር ውስጥ ዋሻ ተጉዞ አንድ ሺ ሜትር ቁልቁል ተምዘግዝጎ ኃይል የሚያመነጨውና የሰው ልጅ ከፈተኛ ጥበብና ስልጣኔ የታየበት የግልገል ጊቤ ቁጥር ሁለት ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የሚጥቀሱ ናቸው፡፡ የአምባርቾ 777 ደረጃ ኢኮቱዝም ስፍራ፣ የገመሻ ሀምባርቾ ፍል ውሃ፣ ኢባላ ፍል ውሃ ሀላባ ዞን የሚገኘው አርቶ ፍል ውኃ፣ የቦዮ ሐይቅ፣በስልጤ ዞን የሚገኘው የሀሮሸይጣን ሀይቅ፤ ትንሹ አበያ ሐይቅና ሌሎችም ለቱሪዝም አገልግሎት መዋል የሚችሉ መስህቦች በክልሉ ይገኛሉ፡፡

በክልሉ አንድ ብሔራዊ ፓርክ ማለትም ጊቤ ሸለቆ ብሔራዊ ፓርክ የሚገኝ ሲሆን ፓርኩ በውስጡ ብርቅዬ የሆኑና ለቱሪዝም አገልግሎት ከፍተኛ ጠቃሜታ ያላቸው በርካታ ትናንሽ፣ መካከለኛና ትላልቅ የአጥቢ እንስሳት፣ የአዕዋፍትና የዕጽዋት ዝርያዎች መኖሪያ ነው፡፡ ከክልሉ ከላይ የተዘረዘሩትና

ያልተዘረዘሩ እምቅ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ እምቅ አቅም ያለው አከባቢ ነው፡፡

### ባህላዊ መስህቦች

በክልሉ 10 ብሔረሰቦች በጋራ የሚኖሩበት ሲሆን የእነዚህ ብሔረሰቦች ቋንቋ በሶስት የቋንቋ ቤተሰቦች ማለትም ሴማዊ፣ ኩሻዊ እና በኦሟዊ ቋንቋ ቤተሰብ የሚመደቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ክልሉ የባህልና የቋንቋ ብዝሀነት ያለው ክልል ነው፡፡የተለያየ ባህል ቋንቋ አለባበስ፣አመጋገበና የአኗኗር ዘይቤ ያላቸው ህዝቦች የሚኖሩበት ክልል ስለሆነ ለቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ የተመቸ ነው፤

## 3 / ለተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች የገበያና የስራ ቦታ አመቺነት ፖቴንሸል በተመለከተ

አብዛኛው የክልሉ ታታሪ አርሶአደር፤ የከተማ ነዋሪዎች እና የዳያስፖራ ቤተሰቦች የመግዛት አቅም እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሉ ካለው ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ አኳያ ከፈተኛ የህዝብ ክምችትና የመግዛት አቅም ያላቸው ትላልቅ ከተሞች እንደ አዲስ አበባ፤ አዳማ፤ ባቱ፤ ወሊሶ፤ ሞጆ፤ ሶዶ፤ ጅማ፤ ሻሸመኔ፤ ሀዋሳ እና አርባምንጭ ለመሳሰሉት ከተሞች አጎራባች በመሆኑ በአምራች እና በአገልግሎት ሰጪ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች ምርትና አገልግሎታቸው የሚሸጡበት ሰፊ የገበያ እድል ያለበት ቀዳሚ ክልል ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በማእከላዊ ክልል ውሰጥ በሚገኙ ዞኖች ልዩ ወረዳዎችና የከተማ አሰተዳደሮች ለኢንዳስትሪው ዘርፍ ተለይተው የተከለሉ የኢንዳስትሪ ዞኖችና ሼዶች በማቋቋም መሰረተ ልማታቸው እንዲሟላ በማድረግ ለግሉ ዘርፍ እየቀረበ ያለበት ሰፊ እድል የያዘ ከመሆኑም በላይ የግል ህንጻና ሼዶችን ተከራይተው መስራት ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች በክልሉ ባሉ ሁሉም የከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ በመሆኑ የክልሉ ትልቅ የኢንቨስትመንት አቅም ናቸው፡፡ በሆቴልና አገልግሎት ዘርፍ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶችም ቢሆን ዘርፉ ያልተነካና በርካታ እድሎች ያሉት ክልል ነው፡፡ ክልሉ አስተማማኝ ሰላም የሰፈነበት  የህዝቦች አንድነት፣ወንድማማችነትና አብሮነት ለዘመናት የተገነባና ተያይዞ የመጣ በመሆኑ ክልሉ ለኢንቨስትመንትና ቢዝነስ ሥራ አመቺ ነው፡፡

## 4 / በምግብ ማቀነባበር ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀበቶች ክልሉ ያለው ልዩ አቅም

ከፈተኛ የስንዴ አምራች በሆኑት ሙሉ ሀዲያ፤ ስልጤ ከፊል ጉራጌ፤ ሀላባና ከምባታ ዞኖች እንዲሁም በማረቆ ቀቤና እና ጠምባሮ ልዩ ወረዳዎች ለፓስታ ማካሮኒ በስኩትና መሰል ምግቦችን ለማቀነባበር በቂ የኢንዳስትሪ ጥሬ እቃ አቅርቦት ያለባቸው አከባቢዎች ናቸው፡፡ በወተትና የወተት ውጤቶች ማቀነባበር ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በወተት ተፋሰስነት በሚታወቁትና በተመረጡት እንደ ከምባታና ሀዲያ በመሳሰሉት ዞኖች ቢሰማሩ ለሚቋቋመው ኢንዳስትሪ የተሻለ ግብአት ይገኝባቸዋል፡፡ የሚገኝባቸው አከባቢዎች ሲሆኑ የአትክልትና ፍራፍሬ ውጤቶችን በማቀነባበር ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች የጉራጌ፤

የምስራቅ ጉራጌ እና የከምባታ ዞኖች በአንጻራዊነት የተሸለ እድል ያላቸው አከባቢዎች ናቸው፡፡ የዶሮና የእንስሳት ስጋን በመቀነባበር በማሸግ ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የጉራጌ፤ የስልጤ፣ የከምባታና የሀዲያ ዞኖች የቀቤና ልዩ ወረዳ በአንጻራዊነት የተሸለ የኢንዳስትሪ ጥሬ እቃ ግብአት ለማቅረብ ምቹ አከባቢዎች ናቸው፡፡

## 5/ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የግብርና ምርቶች ለሚሰማሩ

### የዕጸ-ጣእም (መአዛማ ዘይቶች) ልማት

ዕፀ-ጣዕም፣ መዓዛማ እና የመድሀኒት እጽዋቶች ከሆርቲካልቸር ዘርፍ በአነስተኛ መጠን ከፍተኛ ዋጋ ካላቸው የግብርና ምርቶች መካከል ሲሆኑ በአለም የግብርና ምርቶች ግብይት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እየያዙ መጥተዋል፡፡ በአለም ደረጃ የነዚህ ምርቶች ፍላጎትና አጠቃቀም በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ሲሆን ምክንያቶቹ ደግሞ የምግብ ማቀነባበርያ ኢንዱስትሪዎች የቴክኖሎጂ እድገት ማሳየት፤ መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸው የአለማችን ህዝቦች እየጨመረ መሄድ፤ የከተሜነት መስፋፋትና ይህንን ተከትሎ የአመጋገብ ለውጥ መምጣት ዋነኛዎቹ ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ የተዘጋጁ ምግቦች ፍላጎት በከፍተኛ መጠን በመጨመሩ በምግብ ማቀነባበርያ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለጣዕም፣ ለመዓዛና ምግብ ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ ለማቆየት የዕፀ-ጣዕም (መአዛማ ዘይቶች) ውጤቶች አቅርቦትና ግብይት በከፍተኛ መጠን እንዲጨምር አድርጓል፡፡ በክልሉ ከሚገኙ እጽዋት መካከል ጦስኝ፣ አሪቲ፣ ጤና አዳም፣ በሶቢላ፣ ሮዝሜሪ፣ ጠጅሳር፣ ናና፣ ኮሰረት፣ እና የመሳሰሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

በክልላችን እነዚህን እጽዋቶች ለማልማት የሚያስችል ምቹ የአየር ንብረት ሁኔታና ተስማሚ የአፈር አይነት ያለ እና በአነስተኛ ማሳ እና በቀላል አሰራር ከፍተኛ ገቢ ሊያስገኝ ሚችል ምርት በመሆኑ በሁሉም የክልሉ አከባቢዎች ሊመረቱ የሚችሉ በመሆኑ እንደ እምቅ የኢንቨስትመነት አማራጭ መውሰድ ይቻላል፡፡

### 5.1 የአበባ ልማት

በማእከላዊ ኢትዮጲያ ክልል ለአዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ ካለው ቅርበት እንዲሁም ክልሉ ለአበባ ልማት ካለው ምቹ አግሮኢኮሎጂ አንጻር ከታየ ለአበባ ምርት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትም ይሆን አበባን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ፍጹም ተመራጭ መሆኑ በጉራጌ ዞን ውስጥ እየተከናወኑ ያሉ የአበባ ልማቶች በቂ ማሳያ ናቸው፡፡ በመሆኑም መንግስት ለዘርፉ የሰጠውን ልዩ ትኩረት ከግምት ውስጥ በማስገባትና ለአውሮፓ እና ኢስያ ገበያ ያለንን ቅርበት በመገንዘብ በዘርፉ ለሚሳተፉ የግል ባለሀብቶች ትልቅ የውጭ ገበያ እድል ያለው የኢንቨስትመንት ዘርፍ ነው፡፡

### 5.2/ የእንስት ተክል ልማት

እንሰት በክልላችን በሁሉም ደጋማና ወይና ደጋማ እንዲሁም በቆላማ አካባቢዎች በስፋት የሚመረትና እንደ ዋና ምግብነትም የሚያገለግል ተክል ነው፡፡ ስለሆነም የእንሰት ውጤትን በተሻሻለ ሁኔታ በማዘጋጀት ቆጮን እና ቡላን አጥቦና አድርቆ በዱቄት መልክ በማሸግ፣ የእንሰት ስታርች በማዘጋጀት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ በማቅረብ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ከፍ ያለ አዲስ ቢዝነስ እድል አላቸው፡፡ ከእንሰት የሚገኘው ተረፈምርት/ቃጫ/ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፡፡

### 5.3 በሌሎች የኢንቨስትመንት አማራጮች መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች

#### የኢንዳስትሪ ዘርፍ

- ስጋና የስጋ ውጤቶችን ማቀነባበር፤
- አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበር
- የምግብ ዘይት ማቀነባበር
- ፓስታና ማካሮኒ ማቀነባበር፤
- አዮዲን የተጨመረበት ጨው ማምረት፤
- ተቆልቶ የተፈጨ ቡና ወይም የሚሟሟ ቡና ማምረት፤
- የእንስሳት መኖ ማቀነባበር፤
- የመጠጥ ኢንዳስትሪ ማቋቋም፤
- የተለያዩ የጨርቃጨርቅ ጭረቶችን ማዘጋጀት፤መፍተል፣መሸመን፣ማጠናቀቅና ማተም፤
- ቆዳና ሌጦ ማለስለስ ማጠናቀቅ እና ማተም፤
- የቆዳ ውጤቶችና ተጓዳኝ አካላትን ማምረት፤
- የቆዳ ወይም የቆዳ ምትክ ጫማ ማምረት፤
- የእንጨት ውጤቶች ኢንዳስትሪ ማቋቋም፤
- የማተሚያ ኢንዳስትሪ መቋቋም
- የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ኢንዳስትሪ ማቋቋም፤
- የመሰረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ፋብሪካ ማቋቋም፤

- ብረት ያልሆኑ የማእድን ውጤቶች ኢንዳስትሪ ማቋቋም ለአብነት መስታወተወ/የሴራሚክ ውጤቶች፡፡
- የመሰረታዊ ብረታ ብረት ኢንዳስትሪ ማቋቋም፤
- ለስትራክቸር የሚያገለግሉ የብረታ ብረት ውጤቶች ኢንዳስትሪ ማቋቋም፤
- የኮምፒውተር፤የኤሌክትሮኒክስ እና የእይታ እቃዎች ኢንዳስትሪ ማቋቋም፤
- የማምረቻ/አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎችና ዕቃዎች ኢንዳስትሪ ማቋቋም፤
- የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረት
- የእደ ጥበብ፣የገጸበረከት እቃዎች፤አርቴፊሻል ጌጣጌጥ የሙዚቃና የስፖርት እቃዎች ማምረት

**ግብርና ዘርፍ**

- የሀር ትል ማምረት፤
- በስው ሰራሽ ኩሬ አሳ ማምረት፤
- በምርጥ ዘር ብዜት፤
- በእንሰሳት እርባታና ማደለብ፤
- በደን ልማት፤

**አገልግሎት ዘርፍ**

- የኮከብ ደረጃ ያለው ሆቴል፣ሪዞርት፣ሞቴል፣ሎጅ
- የኮከብ ደረጃ ያለው ሪስቶራንት፣
- የአስጎብኝነት አገልግሎት፤
- ትምህርትና ስልጠና ከመዋእለ ህጻናት እስከ ቴክኒክና ሙያ፤
- የጤና አገልግሎት ከክልኒክ እስከ ቴርሸሪ የልዩ ሆስፒታል አገልግሎት፤

እናም በሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች የግል ባለሀብቱ በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መዋእለ ንዋዩን ቢያፈስ በእጅጉ ሀገሩንና እራሱን ሊጠቅም ይችላል ብለን በጽኑ እናምናለን፡፡

*የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት*

*ሆሳዕና ፡-*